# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** ABA-RC, BLB, IGP-RA, IGT-RA, IIB, ITA-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** ዋና የአካዳሚ ኦፊሰር

## የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ እና ምርጫ

I. **ዓላማ**

ዋናዎቹን የትምህርት ቁሳቁሶችና ተጨማሪ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እና የኤተመጻሕፍት (ላይብራሪ) ቁሳቁሶችን የመገምገም እና የመምረጥ አሠራር ሂደቶችን መመሥረት።

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወላጆች/አሳዳጊዎች፣MCPS ተማሪዎች፣ እና/ወይም ሰራተኞች ቀደም ሲል የሚሠራባቸው የማስተማሪያ እና የቤተመፃህፍት ቁሳቁሶች MCPS ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በሜሪላንድ ህግ መሰረት እንደገና የሚገመገምበት ሂደት መዘርጋት።

II. **ትርጉም**

A. ዋነኞቹ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ማለት በኮርስ ወይም በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ለተማሪዎች ዋና የትምህርት መስጫ ወይም የጥናት መገልገያነት በመጠቀም ለተማሪዎች እንደ ዋና የትምህርት ምንጭነት እንዲጠቀሙባቸው የተዘጋጁ የትምህርት ቁሳቁሶች ናቸው።

B. ተጨማሪ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ማለትየማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማሟላት ወይም ለመደገፍ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው።

C. MCPS ደንብ ITA-RA መሠረት፥ የቤተ መፃህፍት (ላይብራሪ) ቁሳቁሶች ማለት ለትምህርታዊ ስኬት እና ለግላዊ ደስታ ሥነ-ጽሑፍን የማንበብ እና ንባብን ለማድነቅና ለመደሰት የተዘጋጁ የንባብ ቁሳቁሶች ናቸው። የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች በት/ቤት እና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉትን ቤተ-መጻሕፍት ያካትታል። ለትምህርት መስጫነት ጥቅም ላይ የዋሉ ማናቸውም የቤተ-መጽሐፍት ቁሳቁሶች እንደ ማስተማሪያ ቁሳቁስ መገምገም አለባቸው።

III. **የአፈጻጸም ቅደም-ተከተል**

A. አጠቃላይ

1. የመማሪያ ቁሳቁሶች፣ የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት እንደአስፈላጊነቱ የትምህርት ይዘት መምህራን ባለሙያዎች፣ የትምህርት ቤት ቤተ መጻሕፍት ሚዲያ ባለሙያዎች፣ የእያንዳንዱ የትምህርት አከባቢ አስተባባሪ/ሱፐርቫይዘሮች የሥራ መደቡ የሚመለከታቸው የትምህርት ባለሙያዎች አማካይነት መገምገም አለባቸው።

2. OCIP የግምገማ እና የምርጫ ክፍል ሁሉንም ዋና ዋና እና ተጨማሪ የማስተማሪያ እና የቤተ-

መጻህፍት ቁሳቁሶችን ከመገዛታቸው በፊት መገምገም እንዳለባቸው ለ MCPS ቢሮዎች፣ ለትምህርት ቤቶች፣ እና ለፕሮግራሞች መመሪያዎችን ይሰጣል።

3. ዋና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በጊዜያዊነት ለ 30 ቀናት የሚፈቀዱ ሲሆን በዚህ ጊዜ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና በትምህርት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በግምገማ እና ምርጫ ሒደት ላይ ያሉትን ቁሳቁሶች መመርመር ይችላሉ። MCPS ቅጽ 281-15፣ MCPS የትምህርት ቁሳቁሶች መደርደሪያ ዋና የመማሪያ ቁሳቁሶች የ 30-ቀን ግምገማ በመጠቀም አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ። አስተያየቶቹ በሚመለከተው የትምህርት ዘርፍ አስተባባሪ/ሱፐርቫይዘር ይገመገማሉ።

B. ቁሳቁሶችን መለየት

1. ሻጮች/አሳታሚዎች የቁሳቁስ ሽያጭን በተመለከተ በቀጥታ መነጋገር የሚችሉት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ሳይሆን ከግምገማ እና ምርጫ ክፍል ጋር ብቻ ነው። (በተጨማሪ MCPS ደንብ ABA-RCበትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም በአቅራቢያ የሚገኙ ቬንደሮችን ይመልከቱ)። የቁሳቁስ ሽያጭን ለመጠየቅ ሌሎች ሰራተኞችን የሚያነጋግሩ ሻጮች/አሳታሚዎች ወደ ግምገማ እና ምርጫ ክፍል መመራት አለባቸው።

2. MCPS-ሠርተፊኬት ያላቸው ሰራተኞችf በኮንፈረንስ እና ፕሮፌሽናል ዴቨሎፕመንት ወቅት አዳዲስ የታተሙ የማስተማሪያ እና የቤተ-መጻህፍት ቁሳቁሶችን እንዲለዩ ይበረታታሉ።

3. የግምገማ እና ምርጫ ክፍል ሠርተፊኬት ያላቸውን ሰራተኞች በመወከል አዲስ የታተሙ እና የተሻሻሉ የትምህርት እና የቤተ-መጻህፍት ቁሳቁሶችን ቅድመ እይታ እና የግምገማ ቅጂ ለማግኘት ይችላል።

C. የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት በሜሪላንድ ህግ (COMAR)፣ 13A.01.06.03፣ Educational Equity፣መሰረት፣የትምህርት እና የቤተመጻህፍት ቁሳቁሶችን ለመገምገም ት/ቤቶች ፍትሃዊነትን እንዲተረጉሙ ይፈልጋል።የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት፣ እና የባህል ብቃት። ሁሉም ቁሳቁሶች ለተማሪዎች እድሜ የሚመጥኑ፣የመማር ማስተማር ዘይቤን የሚከተሉ፣ እና ቁሳቁሶቹ ለተዘጋጁላቸው ተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና አእምሮአዊ እድገት ተስማሚ መሆን አለባቸው።

1. የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግምገማ

   a) ዋና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች MCPS ቅጽ 365-25 የትምህርት መሣሪያዎች ግምገማ ሪከርድ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ወይም የተለየ ኮርስ ለሚሰጡ ወይም የሥርዓተ ትምህርት ፕሮግራሞች የዲስትሪክት አቀፍ ትምህርት አገልግሎት መርኅን በመጠቀም የግምገማ እና የምርጫ ኮሚቴ ተገምግሞ መመረጥ አለባቸው።

   b) ተጨማሪ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች MCPS ቅጽ 365-25 የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የምዘና ሪከርድ በመጠቀም የሚመለከተውን ባለሙያ አስተማሪን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት ሠርተፊኬት ባላቸው ሰራተኞች መገምገም አለባቸው።

c) የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ለአጠቃላይ MCPS ፕሮግራም አወንታዊ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ እና በቀጥታ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአተ ትምህርት ጋር መጣጣም አለባቸው።

d) በሁሉም የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግምገማ ላይ የሚተገበሩ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው:-

(1) ቁሳቁሶቹ በቀጥታ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ ትምህርት ጋር የሚጣጣሙና ከባህላዊ ብዝሃነት ጋር የሚጣጣሙ እንዲሁም ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች ጋር የማይቃረኑ መሆን አለባቸው።

(2) ቁሶቹ አሉታዊ አመለካከቶችን፣ የተዛቡ አመለካከቶችን፣ ፀያፍ ቃላቶችን፣ አስፀያፊ ትርጉሞችን እና ዘዬዎችን (ከታሪካዊ አገላለፅ ወይም ስነጽሑፋዊ ሁኔታ በስተቀር) ማስወገድ አለባቸው። ነገር ግን፣ ይህ ክልከላ ከቦርድ ፖሊሲ ACA መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ጋር በሚጣጣም መልኩ ለትምህርታዊ ዓላማ እንደዚህ ያሉ ቋንቋዎችን፣ ምስሎችን፣ ወይም ምልክቶችን ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ መወያየትን ለመከላከል ጥቅም ላይ አይውልም።

(3) ቁሳቁሶቹ በአግባቡ ተማሪዎች ማህበራዊ ጉዳዮችን እንዲመረምሩ፣ እንዲተነትኑ፣ እና እንዲገመግሙ እድል ይሰጣቸዋል።

(4) የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የሚከተሉትን ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው:-

(a) የዕድሜ/የክፍል ደረጃ አግባብነትን በማመጣጠን (Motion Picture Movie Association ሲተገበር የዕድሜ ደረጃዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው)

(b) የቅርብ ጊዜ ከሆነ – የቅጂ መብት

(c) ግልጽነት፣የተመጠነ፣ እና ለግንዛቤ የማያስቸግር

2. የአጠቃላይ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ቁሳቁሶች ግምገማ

MSDE አጠቃላይ የጤና ትምህርት ስርአተ ትምህርት የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ የጾታ ግንኙነትን የሚመለከቱ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችበስቴት ህግ እና MCPS ደንብ IGP-RA አጠቃላይ የጤና ትምህርት መማሪያ ፕሮግራም መርኅ መሠረት ተገምግመው ጸድቀዋል።

3. የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ

a) የቤተ-መጻህፍት ቁሳቁሶችን ገምግሞ ለማጽደቅ ዳታቤዝ የተጠያቂነት መሥፈርት በመጠቀም አንድ የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስት እና ሠርተፊኬት

ያለው ሰራተኛ (ለምሳሌ፦ የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት ሚዲያ ባለሙያ፣መምህር፣ አስተዳዳሪ) መገምገም እና መፈረም ይኖርባቸዋል።

b) የትምህርት ቤት ቤተ መፃህፍት የሚዲያ ስፔሻሊስቶች የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶችን ለመገምገም ፕሮፌሽናል የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት ግምገማ ጆርናሎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

c) አዲስ የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት ቁሳቁሶችን በሚገመግሙበት ጊዜ የሚከተሉት መመዘኛዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፦

(1) ሥርዓተ ትምህርቱን የሚደግፉ እና የሚያበለጽጉ መሆናቸውን

(2) የተማሪዎችን ግላዊ ሁኔታ እና የትምህርት ፍላጎት እንደሚደግፉ

(3) በተለያየ የስነ-ጽሁፍ አቀራረብ ትክክለኛነትን፣ስነጥበባዊ እና የጥራት ደረጃዎች መሥፈርትን የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

d) በግምገማ እና በምርጫ ሂደት ለተወሰኑ አጠቃቀሞች ብቻ እስካልተመደቡ ድረስ፥ ሁሉም ተማሪዎች ለነጻ ምርጫ ወይም ለግል ንባብ ወይም ጥናት መምረጥ ይፈቀድላቸዋል። የቤተ መፃህፍት ቁሳቁስ ደራሲያንን፣ ዘውጎችን ወይም ሌሎች የሊተርሲ ፕሮግራሞችን ለማሳደግ እንደ አንባቢ ድምጽ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

D. ቀደም ሲል የጸደቁ የማስተማሪያ እና የላይብረሪ ቁሳቁሶች ግምገማ

1. OCIP የትምህርት ይዘት ስፔሻሊስቶች እና የት/ቤት ሰራተኞች ከስርአተ ትምህርት አላማ ጋር የተሣለጠ ክለሳ፣ የትምህርት ቁሳቁስ የጊዜ ገደብ፣ የታተሙ የትምህርት ቁሳቁሶች ያለቁ መሆናቸውን፣ ትክክለኛነታቸውን፣ እና በንፅፅር የገበያ ዋጋዎቻቸው ላይ በመመሥረት የትምህርት ቁሳቁሶችን በሙሉ በቀጣይነት ይገመግማሉ።

2. እያንዳንዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ ከሌሎች ሠርተፊኬይ ያላቸው ሰራተኞች ጋር በመሆን የትምህርት ቤቶችን የሚዲያ ማእከል ቁሳቁሶች ክምችት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመግማሉ።

E. ቀደም ሲል ስለጸደቁት ዋና ዋና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና ተጨማሪ ለትምህርት ድጋፍ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን እና የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶችየስጋት መፍትሔ

1. የወቅቱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች፣ የወቅቱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተማሪዎች ያሏቸው ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሰራተኞች በየትምህርት ቤታቸው ስለሚጠቀሙባቸው ዋና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ወይም ተጨማሪ የትምህርት መርጃዎችን ወይም የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶችን በሚመለከት የሚኖራቸውን ጥያቄ (ለሚመለከተው መምህር ወይም የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ) ማቅረብ አለባቸው። በመምህሩ ወይም በትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ ያልተፈቱ ስጋቶች ለትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር መቅረብ አለባቸው።

a) በተለይም አሳሳቢውን ነገር ከተፈቀደለት አላማ ውጭ ለሌላ ዓላማ ስለመጠቀም ወይም ስለ ቁሳቁሱ ከሆነ ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ የስጋቱን መፍትሔ ለመወሰን ውይይቶችን ማመቻቸት አለበት። የግምገማ እና የምርጫ ክፍል ርእሰመምህሩን/ተወካዩን ለመደገፍ ይገኛሉ።

b) የትምህርት መርጃው ከተፈቀደለት በተለየ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ የግምገማ እና ምርጫ ክፍል አስተባባሪው፣ ርእሰመምህሩ በትምህርት ቤት ድጋፍና ማሻሻያ ጽ/ቤት እና/ወይም በጽህፈት ቤቱ ውስጥ የሚመለከተውን ሰራተኛ በመመደብ የስርአተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች (OCIP) የተፈቀደውን የቁሳቁስ አጠቃቀም ችግር በመፍታት ይረዷቸዋል።

2. ቁሱ በተፈቀደው መሠረት ጥቅም ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ፣ የግምገማ እና ምርጫ ክፍሉ ለተጨማሪ መፍትሄ እና ቁሳቁሱ(ቹ) እንደገና እንዲታዩ OCIP ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ጉዳዩ የሚመለከተው ተወካይ ነው።

F. የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶችን እንደገና ማጤን

1. ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ዳግመኛ የተገመገሙ ማናቸውም ቁሳቁሶች እንደገና አይገመገሙም።የቀድሞው ውሳኔ ይፀናል።

2. በተቃውሞ ምክንያት እየተገመገሙ ያሉ ቁሳቁሶች የግምገማው ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ ለተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ጥቅም ላይ እንዲውል የሚሪላንድ ህግ ይፈቅዳል።

3. የማስተማሪያ ቁሳቁስ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ዳግመኛ ያልተገመገመ ከሆነ፣ አስተባባሪው(ዋ) –

a) ፋይል ከፍተው ከርዕሰ መምህር ወይም ከትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሞያዎች ጥያቄውን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችን በሙሉ ይጠይቁ በአግባቡ መሠረት ጉዳዩን ለመፍታት ያደረጉትን ጥረት እና የደብዳቤ ልውውጦችን ይመልከቱ፣ እና

b) ግለሰቡን በማነጋገር ጉዳዩን በትብብር እና በውይይት ለመፍታት እና የችግሩን ማቅለያ ዘዴዎች መፍትሄ ለማግኘት ተነጋገሩ።

4. ይህ መደበኛ ያልሆነ ሂደት ምንም አይነት ቅጾች ወይም መደበኛ ሰነዶች አያስፈልጉትም። ነገር ግን አስተባባሪው(ዋ) ከግለሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት እና ችግሩን ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት መዝግቦ መያዝ እና ማቆየት አለበት። እና እርዳታ ለማግኘት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት የሚላክ/የሚተላለፍ ማንኛውንም ነገር ማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል።

5. ከግምገማ እና የምርጫ ክፍል አስተባባሪ ዘንድ ውሳኔ ካልተገኘ፣ ግለሰቡ(ቧ) MCPS ቅጽ 281-18፣MCPS የትምህርት እና/ወይም የቤተ መፃህፍት እቃዎች እንደገና እንዲፈተሽ ወይም እንደገና እንዲታይ ሊጠይቅ ይችላል።

6. የግምገማ እና ምርጫ ክፍል አስተባባሪ ቅጹን በተቀበለ(ች) 10 የስራ ቀናት ውስጥ–

a) የቀረቡትን ጥያቄዎች በተመለከተ ማንኛውንም ጥያቄዎች ለማብራራት እንደገና እንዲታይ ከጠየቀ(ች)ው ግለሰብ ጋር የስብሰባ ቀጠሮ መያዝ ይችላል፣

b) ጽሑፉን በድጋሚ እንዲመረምር፣ ኮሚቴው ሥራውን የሚያጠናቅቅበትን ቀን ለመወሰን ጊዜያዊ የግምገማና አስመራጭ ኮሚቴ ይሰይማል፣ እና

c) የሚወስደውን ያህል ጊዜ ግምቱን ለግለሰቡ ማሳወቅ ያስፈልጋል።

7. አስተባባሪው(ዋ)–

a) እንደአስፈላጊነቱ የት/ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ(ዎች)፣ አስተማሪ(ዎች)፣ ርእሰ መምህር፣ አማካሪ(ዎች)፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አስተባባሪ(ዎች) እና አንድ የህዝብ ሴክተር የቤተ-መጻህፍት ባለሙያን ያካተተ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ለምሳሌ፡- ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተ መፃህፍት፣ እና/ወይምሙያዊ ሰራተኞችን ያቀፈ ኮሚቴ ጋር ስብሰባ ያደርጋል።

b) በኮሚቴው የተጠየቀውን ማንኛውንም ተጨማሪ ጥናት ያካሄዳል።

8. ኮሚቴው –

a) የግምገማው ርዕሰ ጉዳይ የሆነውን ቁሳቁስ፣ የቀረበውን ሰነድ፣ እና ኮሚቴው ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም ሰነድ ይመረምራል፤ እና

b) ለኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ መነሻ የሆነውን OCIP ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት እና ዋና አካዳሚክ ኦፊሰር የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባሉ፣ ግምገማ እንዲደረግ በቀረበው ጥያቄ የተነሱትን ስጋቶች በቀጥታ እና በግልፅ ያቀርባል፣ እና አስተያየቱ ትኩረት የተደረገበትን ቁልፍ መረጃ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል።

9. OCIP ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት እና ዋና አካዳሚክ ኦፊሰሩ የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ ይገመግማሉ፣ ስለ ቁሳቁሱ ውሳኔ ይሰጣሉ፣ እና ውሳኔያቸውን ለግለሰቡ(ቧ) በጽሁፍ ያሳውቃሉ።

a) ሊሆኑ የሚችሉ ውሳኔዎች የቁሳቁሱን ቀጣይ አጠቃቀም ለማረጋገጥ፣ ስለ ዕቃው ቀጣይ አጠቃቀም የተፈቀዱና የተመረጡ ኮርሶችን ወይም የተማሪዎችን ዕድሜ የሚመጥኑ ሁኔታዎችን ግልጽ ማድረግ፣ ወይም ቁሱ ጥቅም ላይ እንዳይውል ማድረግን ሊያካትቱ ይችላሉ፥ ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

b) የሚመለከታቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ ርዕሰ መምህር፣ ወይም የት/ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያን ጨምሮ፣ በድጋሚ እንዲፈተሽ ስለታሰበው ቁሳቁስ እና ስለ ግምገማው ውጤት በጽሁፍ ይነገራቸዋል።

10. ግለሰቡ(ቧ) ውሳኔውን ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማለት ይችላል/ትችላለች።

H. ይግባኝ

1. ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርብ ይግባኝ

የዲስትሪክት ኦፕሬሽን ጽ/ቤት የይግባኝ ዲቪዥዮን ስለ ዋና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና ተጨማሪ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን እና የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶች በሚመለከት ለዋና የአካዳሚክ ኦፊሰር ውሳኔዎች ሱፐር ኢንተንደንቱን ወክሎ ይሠራል። የዋና አካዳሚክ ኦፊሰር ውሳኔ ይግባኝ ለማለት፣ ውሳኔው ይፋ በተደረገ 15 ቀናት ውስጥ ይግባኝ አቅራቢው ለይግባኝ ተቀባይ ክፍል ማቅረብ ይችላል።

2. ለትምህርት ቦርድ የሚቀርብ ይግባኝ *መመሪያ* BLB፣ ስለ ይግባኝ እና የችሎት አሰራር ህጎች

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ሊባል ይችላል፣ በቦርድ ፖሊሲ BLB፣ የይግባኝ እና የችሎት አሰራር ደንቦች

***ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፦*** የተብራራ የሜሪላንድ የትምህርት ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ 4-142፣ 7-106፣ እና 7-910፣ የሜሪላንድ የትምህርት ኮድ ደንቦች፡ 13A.01.06.03, 13A.05.02.13.H እና M, 13A.06.06 እና 13A.09.10.13.

**የደንቡ *ታሪክ፦*** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 3652 የፀደቀው ኦክቶበር 16 ቀን 1980 ዓ.ም. ነው፣ኖቬምበር 23 ቀን 1999 ተሻሽሏል፣ የወቅቱ የቢሮ ስያሜ ጁን 1, 2000 ተሻሽሏል፣ ሴፕተምበር 20 ቀን 2005 ስለ COMAR ቴክኒካዊ ማሻሻያ ተደርጓል፣ ማርች 29, 2023 ተሻሽሏል። ሴፕቴምበር 9, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መግለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

<table>
<tr><th>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</th><th>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</th></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024